# በኢትዮጵያ የሠላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች (ኢሠዴአኃ) ም/ቤት
# ለሁለተኛው የፓሪስ የተቃዋሚ ድርጅቶች ስብሰባ የቀረበ ሰነድ

## መግቢያ

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የታደለች አገር እንደመሆኗ በልማትና ሥልጣኔ እየተጠራች አይደለም። ይልቁንም በረሃብና ተመጽዋችነት መጠራት ከጀመረች አያሌ አሥርተ-ዓመታት ተቆጥረዋል። ለዚህ አገራችን በባዕዳን ኃይሎች ከሚቃጣ ወረራና ከሚውጠነጠን ሴራ፤ በውስጥም ከሚካሄድ የእርስ በርስ ጦርነት ነፃ ሆኖ በልማትና ዕድገት ላይ ሙሉ ኃይሏን ለማዋል ያለመቻሏ አስተዋጽኦ አድርጓል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሠላማዊ የሥልጣን ሽግግርና የሥርዓት ለውጥ እንዲሁም ለዴሞክራሲ ያደረገው ትግል እስከዛሬ ፍሬ አልሰጠም። የሩቁን ትተን የ1966 ዓ.ምን ሕዝባዊ አብዮት ብንመለከት እንኳ ደርግ በግርግር ሥልጣን ጨብጦ የሕዝብን ጥያቄ ለማፈን ጥሯል። ከርሱ የተለየ የፖለቲካ አጀንዳ ይዘው የተነሱ የፖለቲካ ድርጅቶችን አንድም በራሱ ኃይል ያሊያም እርስ በርስ በማጋጨት ከፍተኛ ጥፋት አስከተለ እንጂ በቀና መንፈስ አልተመለከተም። በደርግ እግር የተተካው የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥትም በባዕዳን ድጋፍ በሽግግሩ ሂደት ሁሉም ተቃዋሚዎች እንዳይሣተፉ በማድረግ በጉጉት የተጠበቀውን ሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ የሥልጣን ሽግግር ተስፋ አጨልሞታል።

በሽግግሩ ወቅት የተከሰተው ሁኔታ በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የሽግግሩን ሂደት የመመርመር ጥያቄ በመፍጠሩ በፓሪስ ተሰብስበው ወያኔ/ኢሕአዴግን የሚያካትት የሠላምና ዕርቅ ጉባዔ በአዲስ አበባ እንዲካሄድ ወሰኑ። ሁሉም የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ ሙያ ማኅበራት፤ ሲቪክ ድርጅቶች፤ የኢኮኖሚ ተቋማት ጥሪውን ሲቀበሉ ወያኔ/ኢሕአዴግ ግን ጥሪውን ካለመቀበል አልፎ ጉባዔውን ለማደናቀፍና የጉባዔው ውሣኔ ተግባራዊ እንዳይሆን እንቅፋቶች ፈጥሯል። ከጉባዔው ጋር በተያያዘ ዜጎች ታስረዋል። ድርጅቶች ከሽግግሩ ም/ቤት ተባረዋል።

ሆኖም ጉባዔው በአዲስ አበባ ከታኅሣሥ 9-13, 1986ዓ.ም. በተሣካ ሁኔታ ተከናውኖ በተቃዋሚዎች መካከል ሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ አማራጭ የትግል ትብብር አስፈላጊነት በመቀበሉና ለዚህም አንድ ም/ቤት እንዲቋቋም በመወሰኑ በጉባዔው ተሣታፊዎች የኢትዮጵያ የሠላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች (ኢሠዴአኃ) ም/ቤት ተቋቁሟል።

## ክፍል -1- የኢሠዴአኃ ም/ቤት እንቅስቃሴ

ከምሥረታው ጀምሮ ያልተወደደው የኢሠዴአኃ ም/ቤት በኃይል ብቻ በሚያምነው ወያኔ/ኢሕአዴግ የሚያወጣውንና የሚፈጽመውን አፍራሽ ፖሊሲዎች እንዲመረመርና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ራሱን እንዲያዘጋጅ የሚቻለውን ትግል አድርጓል።

ም/ቤቱ የሚደርስበትን ግልጽና ሥውር ተጽዕኖዎችን በመቋቋም ሕዝባዊ የተቃውሞ ስብሰባዎችን የሕዝብ ውይይት መድረኮችን፤ የም/ቤቱ ልሣን 'አማራጭ'ን፤ የአቋም መግለጫዎችንና ይፋ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን በመጠቀም ትግል አድርጓል።

ገዢው ፓርቲ ም/ቤቱ የሚያቀርባቸውን ጥያቄዎችና የሚያሰማቸውን ተቃውሞዎች ለአፍራሽ ፕሮፓጋንዳ ቢጠቀምም ግልጽ ያልወጡ የማስተካከያ እርምጃዎች ለመውሰድ የተገደደባቸው ሁኔታዎች መኖራቸው ተስተውሏል።

በተለያዩ ምክንያቶች የተፈለገውን ያህል አይፈፀም እንጂ ም/ቤቱ በመዋቅሩ መሠረት በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ለማደራጀት ሰፊ ጥረት አድርጓል። በአገር

ውስጥ የም/ቤቱ የወጣቶች ክንፍ ተደራጅቶ በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኝ ሲሆን የሴቶች ክንፍ ለመመሥረት በዝግጅት ላይ ይገኛል።

ከአገር ውጪ ያለው የም/ቤቱ እንቅስቃሴ የሚያመረቃ ባይሆንም የሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች እንቅስቃሴዎችን የመከታተልና የኢትዮጵያን ጉዳይ በሚመለከቱ ጉባዔዎችና ስብሰባዎች የመሣተፍ እንቅስቃሴ አድርጓል። የነዚህ እንቅስቃሴዎች መሠረት በአገራችን ለሚደረገው ትግል የመጀመሪያው እርምጃ ለሌሎች አክብሮት መስጠትና በተወሰኑ ድርጅቶች ብቻ ለችግሮቹ የተዘጋጀ ዘላቂ መፍትሄ ሊቀርብ አይችልም የሚለው የም/ቤቱ እምነት ነው።

የኢሠዴአኃ ም/ቤት በአገር ውስጥና በውጪ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች በመንግሥት ከሚደርስበት ውስብስብና መጠነ ሰፊ ተጽዕኖ ተጨማሪ ችግሮች አጋጥመውታል። ለዚህም ሁለት አቢይ ምክንያቶች አሉት። የመጀመሪያው የደርግ መንግሥት የተለያየ አጀንዳ ካላቸው የፖለቲካ ኃይሎች ጋር ተቀራርቦ ከመነጋገር ይልቅ የኃይል እርምጃ በመምረጡ በርካታ ኃላፊነት ሊሸከም የሚገባው የትውልድ ጭማቂ ወጣት ደም ያለፍሬ በአደባባይ መፍሰሱና በወጣቱ የትግል ተነሣሽነት ላይ ያሣደረው ተጽዕኖ ነው። ሁለተኛው በተቃዋሚ ኃይሎች መካከል በመቻቻል የትግል ኅብረት መፍጠርና ማጠናከር ያለመቻሉ ሲሆን ይህ በሁላችንም ቢነገርም፤ በየአደባባዩ ቢስተጋባም ከግልና የቡድን ስሜት በመነሣት በሚደረግ ያልተቀናጀ ሩጫ ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም። በዚህ ረገድ ከኢሠዴአኃ ም/ቤት ምሥረታ ማግሥት ጀምሮ የተሞከሩትን አፍራሽ እንቅስቃሴዎች ለመዘንጋት ጊዜው በጣም ቅርብ ነው።

## ክፍል -2- የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ

### 2.1. አጠቃላይ

ያለንበት ወቅታዊ ሁኔታ ካሣለፍነው ታሪካችን የሚለየው አንድ አብይ ጉዳይ አለ። ይህም ከወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በፊት ባዕዳን ለሥውር ተልዕኮአቸው በመንግሥት ደረጃ የተመቻቸ ሁኔታና አጋጣሚ አላገኙም ነበር። ይሁን እንጂ ዛሬም አገራችን ከገጠማት ፈታኝ ሁኔታ ሊታደጓት የሚነሱ ቆራጥ ልጆች መካን አልሆነችም። ከሕዝብና ከተቃዋሚ ድርጅቶች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ገዢው ፓርቲ ለመስማት ባለመቻሉ ወይም ባለመፈለጉ ከጦርነት አዙሪት ልንወጣ አልቻልንም። በአራቱ ማዕዘናት የባሩድ ሽታ ስለመኖሩ ከተለያዩ ምንጮች እንሰማለን። ዛሬም እነዚህ ጥያቄዎች ሰሚ ጆሮ አልተቸሩም።

በመሆኑም የተቃዋሚ ድርጅቶች የመንቀሣቀስ መብት፤ የሙያ ማኅበራት በነፃ የመደራጀት መብት፤ የነፃው ፕሬስ እንቅስቃሴ፤ የሕዝብ ኃሣብን በነፃ የመግለጽና በመረጠው ድርጅት ሥር የመደራጀት መብት ዛሬም በወያኔ/ኢሕአዴግ አልተጠበቀም። በሕዝብ መካከል መተማመን ለማጥፋት የተጀመረው በዘርና በቋንቋ የመከፋፈል ጥረት እንደቀጠለ ነው።

### 2.2. ጦርነትና ግጭት

በአሁኑ ጊዜ የሰሜኑ የአገራችን ክፍል የጦርነት ቀጠና ሆኗል። የንጹሃን ዜጎች ሕይወት በጥይትና ክላስተር ቦንብ ተሰልቧል፤ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ተፈናቅለዋል፤ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ልማት ተቋማት ፈርሰዋል፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ለሥነ ልቡና ውጥረት ተዳርጓል። በተጨማሪ ሕዝቡ ጦርነት የሚጠይቀውን ሁሉ የሚያቀርብበት ሁኔታ ውስጥ ነው። በግንባር ተሰልፏል፤ በደጀንነትም እያገዘ ነው። የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥትም ለልማት ሊውል የሚችለውን ጊዜ፤ ኃብትና የሰው ኃይል ጦርነቱን ለመከላከል በማዋል ላይ ነው።

ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችም ከመንግሥት ጋር ያላቸውን ልዩነቶቻቸውንና የደረሰባቸውን ወደኃን በመተው ጦርነቱን አውግዘዋል። አገራችን ከጦርነቱ እንድትወጣና ችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኙ የበኩላቸውን ለማበርከት ኃላፊነት የተሞላበት ጥያቄ በማቅረብ ላይ ናቸው። በተለይ የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር (አርዱፍ) የወሰደው የአንድዮሽ የተኩስ ማቆም እርምጃ የሚደነቅ ነው።

በሌላ በኩል በየአቅጣጫው ከሚሰማው የጥይት ድምጽ በተጨማሪ በደቡብ ኢትዮጵያ በጎጂ ኦሮሞና በጌዲኦ ሕዝቦች መካከል ግጭት ተፈጥሯል። ግጭቱ በሺ ለሚቆጠሩ ዜጎች ሕልፈት፤ በመቶ ሺ ለሚቆጠሩ መፈናቀል፤ ከፍተኛ ግምት ላለው ንብረት ውድመት ምክንያት

ሆኗል። ይህን ያህል ጥፋት ደርሶ መንግሥት ጉዳዩን ከወር ለበለጠ ጊዜ ይፋ ያለማድረጉ ለሰሚኑ ችግር የተቻለውን ሁሉ ባደረገው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም በደቡብ ተፈናቃዮች አዕምሮ ጥያቄ አስነስቷል።

### 2.3 ማጠቃለያ

በአጠቃላይ በአገራችን በተከሰተው ጦርነት የኢሠዴአኃ ም/ቤት መንግሥት እያደረገ ያለውን ሠላማዊ መፍትኼ የመሻት ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ ቢቀበልም ለጦርነቱ ወቅታዊና ተመጣጣኝ ምላሽ መስጠት እንዳለበት ያምናል። መንግሥት በጦርነቱም ሆነ በግጭቱ የተፈናቀሉ ዜጎች ላይ የሚደርሰው ችግርና እንግልት የሚቀንስበትንና ዜጎች ወደነበሩበት ተመልሰው ኑሮአቸውን የሚመሩበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ያምናል። ከጦርነቱ ጋር በተዛመደ ሁኔታ ከሚኖሩበት እንዲወጡ የሚደረጉ ዜጎች ሰብዓዊ መብታቸውና ክብራቸው እንዲጠበቅ ከሁለቱም ወገኖች ጥረት እንደሚያስፈልግ የኢሠዴአኃ ም/ቤት ያምናል። በሁለቱም ወገኖች ሥር የሚገኙ የጦር ምርኮኞች ያሉበት ሁኔታ በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት ለዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ግልጽ መሆን እንዳለበት [redacted]ያስገነዝባል የውጭ መንግሥታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው ሪፖርቶችና የሚወስዷቸው አቋሞች ሚዛናዊና ሁለቱም ወገኖች ሠላማዊ መፍትኼ እንዲያመጡ የሚያደርጉ መሆን እንዳለባቸው ይጠበቃል። ሆኖም በአሁኑ ጊዜ ከነዚህ የሚሰማው ሚዛናዊነቱ የሚያጠያይቅ ሪፖርትና አቋም ኢሠዴአኃ ም/ቤትን ያሳስበዋል።

ይሁን እንጂ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ዛሬም ከሕዝብና ከተቃዋሚዎች የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች ለመመለስ ቀርቶ ለማድመጥ አልፈለገም። ጦርነቱን ለመመከትም ይሁን ዘላቂ መፍትኼ ለማምጣት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ግልጽነት ይጎድለዋል፤ ተቃዋሚ ኃይሎችን አላሣተፈም፤ ወታደራዊ እርምጃውም ወቅታዊና ተመጣጣኝ አይደለም። ለጦርነቱና ለተፈናቀሉ ዜጎች የሚደረገው እርዳታ አሰባሰብና ሥርጭት ብሄራዊ ዓላማውን በሚያንጸባርቅ መልክ ማዕከላዊነትን የተከተለ አይደለም። በተለይም ለተፈናቃዮች በሚደረገው ዕርዳታና መልሶ ማቋቋም አድሎአዊነት ይታያል።

የኢሰዴአኃ ም/ቤት በእነዚህ ሁኔታዎች የበኩሉን እርምጃና አቋም ወስዷል። ከፍተኛ የሕዝብ ዕልቂት፣ መፈናቀልና የንብረት ውድመት ያስከተለውን በሻዕቢያ የተጫረ ጦርነት አውግዟል። ምላሽ ባይሰጠውም ም/ቤቱ በአገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ ዙሪያ መንግስት ከሕዝቡና ከተቃዋሚዎች ጋር የሚመክርበትን ሁኔታ እንዲያመቻች በተደጋጋሚ በደብዳቤ ጠይቋል። ከሕዝብና ከአለም አቀፍ ኅብረተሰብ እንዲደበቅ የተፈለገውን በጌዴኦና በጉጂ ኦሮሞ ሕዝቦች መካከል የተፈጠረውን ግጭትና ያስከተለውን ጉዳት አጋልጧል። ልሣኑ በሆነው አማራጭ ጋዜጣ በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ማብራሪያዎችን በማቅረብ ኅብረተሰቡ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖረው አድርጓል። በማድረግም ላይ ነው።

ዛሬም ሕዝቡና ተቃዋሚዎች ወደ ዘላቂ መፍትሄ የሚያደርሱ ጥያቄዎች ከማንሳት አልተቆጠቡም። ጥያቄዎቹ ለሀገራችን ችግሮች መሠረታዊና ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ብሄራዊ እርቅ ይውረድ በሚለው ይጠቃለላሉ። ለዚህም በፖለቲካ እምነታቸው የተነሣ የታሠሩ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችና አባላት መፈታት፣ የነጻ ሠላማዊ ፖለቲካ እንቅስቃሴ በር መከፈት፣ መሪዎቻቸው በውጭ አገር የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች በአገር ውስጥ በግልጽ የሚንቀሣቀሱበት ሁኔታ መመቻቸት፣ የነጻ ሙያ ማኅበራትና የነጻ ፕሬሶች ከተጽዕኖ ውጪ እንዲንቀሳቀሱ መደረግ፣... የሚሉት ከመንግስት በኩል የሚጠበቁ ማስተማመኛዎች ናቸው።

## ክፍል 3 ሁለተኛው የተቃዋሚ ድርጅቶች ስብሰባ በፓሪስ

### 3.1 የስብሰባው አስፈላጊነት

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የተቃዋሚ ኃይሎች በሽግግሩ ወቅት የነበረውን ሁኔታ በማጤን የሽግግሩን ወቅት ሂደት እንዲመረመር በመጠየቅ የመጀመሪያውን ስብሰባ በዚሁየፓሪስ ከተማ አድርገው ብሄራዊ የሠላምና ዕርቅ ጉባዔ በኢትዮጵያ እንዲካሄድ ወስነው ነበር። በውሣኔው መሠረት ስብሰባውን ለመካፈል ጥያቄ ያቀረቡትና በአስተባባሪው ኮሚቴ ተቀባይነት አግኝተው ከተመዘገቡ ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች፤ የሙያ ማኅበራት፤ የኢኮኖሚ ተቋማትና

ታዋቂ ኢትዮጵያዊያን (በታዛቢነት) አብዛኛው በተገኙበት ጉባዔው በአዲስ አበባ ግዮን ሆቴል ከታኅሣሥ 9-13, 1986 ዓ.ም. በተገቢው መንገድ በተሣካ ሁኔታ ተካሂዶ ባሣለፈው ውሣኔ መሠረት የኢሠዴአኃ ም/ቤት ተቋቁሞ እንቅስቃሴውን ከጀመረ ዓመታት አስቆጥሯል።

የኢሠዴአኃ ም/ቤት ከላይ በተገለጹት የውስጥና የውጭ ችግሮች የተፈለገውን ያህል መንቀሣቀስ ባለመቻሉና የተቃዋሚዎች የትግል ሕብረት መጠናከር በተለይም ባለንበት ወቅትና ሁኔታ ሕዝባዊ ጥያቄ እየሆነ በመምጣቱ ለዚህ የሕዝብ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የዚህ ጉባዔ አስፈላጊነት የሚያጠያይቅ አይደለም። በመጀመሪያው የፓሪስ ስብሰባ ወቅት የተነሱት የዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብት ጥያቄዎችን ዛሬም መልስ አለማግኘታቸው ይህን ስብሰባ አስፈላጊ ያደርገዋል። በተጨማሪ አገራችን ከገባችበት ጦርነትና በሕዝቦች መካከል ከሚፈጠሩ ግጭቶች እንድትወጣና ለችግሩ ዘላቂ መፍትኼ ለማምጣት ተቃዋሚዎች በኅብረት ቆመው ከሕዝቡና ከመንግሥት ጋር የመምከር አስፈላጊነት የሚታለፍ አይደለም።

የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ እርስ በርስ ከመፈራራትና ከመጠላለፍ ይልቅ ተከባብሮና ተፈቃቅዶ መኖር ጠቃሚ መሆኑንና መለያየትም እንደሚታሰበው ቀላል ያለመሆኑን ያመለክታል። ለዚህም በሠላሣ ዓመታት "የነፃነት" ትግል "ነፃ" የወጣችው ኤርትራ ዛሬ "ከቀኝ ገዢዋ" ኢትዮጵያ እንድትለይ በሚደረግ ጊዜ የተፈጠረውን ሁኔታ መመልከቱ ይበቃል።

የደቡብ አፍሪካ ታጋዮች በኅብረት በመታገላቸው፤ ከድል በኋላም ብሄራዊ እርቅ አውርደው ተቻችለው መኖርን በመምረጣቸው የደረሰባቸው ጉዳት የለም። ዜጎች በሙሉ በእኩልነት የሚኖሩባትንና የሚጠቀሙባትን አገር ለመፍጠር ባላቸው ፈቃደኝነት ተባብረው አገራቸውን ይገነባሉ። አገራቸውን ሲገነቡም ዜጎቻቸው የተሻለ የኑሮ ደረጃ ይጠብቃቸዋል።

በአገራችን የፖለቲካ መድረክ ይህ አይነቱ ልምድና እውነታ ተገቢው ግንዛቤ የተሰጠው አይመስልም። በመሆኑም በኢሠዴአኃ ም/ቤት እንቅስቃሴ ላይ ከመንግሥት በተጨማሪ በተቃዋሚ ኃይሎች መካከል ልዩነቶቻቸውን እንደያዙ ተቻችለው የትግል ኅብረት ያለመፍጠር አሉታዊ ተጽዕኖ አሣድሯል።

በመሆኑም የመጀመሪያውን የፓሪስ ስብሰባ ያካሄዱ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁለተኛ የተቃዋሚዎች ስብሰባ ካለፈው በሰፋ ተሣትፎ ለማድረግ ለኢሠዴአኃ ም/ቤት ያቀረቡትን ጥሪ በመቀበል ከአስተባባሪው ኮሚቴ ጋር አስፈላጊውን ግንኙነት አድርጓል። ም/ቤቱ በዙሪያው የታዩት ችግሮች በተለይም በተቃዋሚ ኃይሎች መካከል ያለው የትግል ኅብረት ችግር ተቃሎ ም/ቤቱ ተጠናክሮ እስካሁን በም/ቤቱ ዙሪያ ተሣትፎ ያላደረጉት የሚሣተፉበት ሥልት ተቀይሶ ም/ቤቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በሚፈለገው መጠን በብቃት ለመወጣት የሚያስችል ሁኔታ ይፈጠራል በሚል በስብሰባው ተካፍሏል።

3.2 <u>ቀጣዩ የትግል አቅጣጫ</u>

ሁላችንም እንደምናውቀው የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማድረግ ያስቀመጣቸው ቅድመ-ሁኔታዎች አሉ። እነዚህም በጥቅሉ ሲታዩ ሠላማዊ የትግል መስመር መከተልና በሕገ-መንግሥቱ መሠረት መንቀሣቀስ የሚሉት ናቸው። እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶም ለመንቀሣቀስ ያለው ዕድል የቱን ያህል የጠበበ እንደሆነ ለዚህ ስብሰባ ለማስረዳት አንሞክርም። በአሁኑ ጊዜ በአገራችን በተለያዩ ቦታዎች ሥቃይ እየተቀበሉ ያሉ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና አባላት ከዚህ ውጪ የፈፀሙትን አናውቅም።

በሌላ በኩል ተቃዋሚዎች የሚከተሉትን የትግል አቅጣጫ ስንመለከት በሁለት ይከፈላል። የመጀመሪያዎቹ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ያስቀመጣቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ተቀብለው በሕጋዊ መንገድ ተመዝግበው በአገር ውስጥ የሚንቀሣቀሱት ናቸው። በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደሞከርነው ተቃዋሚን እንደጠላት የሚመለከተው የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት "እንዳያማህ ጥራው፤ እንዳይበላ ግፋው" እንዲሉ እንቅስቃሴአቸውን ገድቦ በፈለገ ጊዜ የተለያየ መሠረተ ቢስ ውንጀላ እየለጠፈባቸው መሪዎቹንና አባላቱን የሚያሰቃይባቸው ናቸው። እነዚህ ወገኖች የሚደርስበቻውን ሥቃይ ተቋቁመው ወያኔ/ኢሕአዴግን በራሱ ሕግና ሕገ-መንግሥት በሠላማዊው የትግል ሥልት ፊት ለፊት የተጋፈጡ ናቸው። ሁለተኛዎቹ አንድም ወያኔ/ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ወደአገር ቤት እንዳይገቡ ያገዳቸው ያሊያም በውጭ

በሚኖሩ ኢትዮጵያያን በደርግ ውድቀት ማግሥት የተመሠረቱ ናቸው። እነዚህ ወገኖች የሠላማዊው ትግል በር ስለተዘጋባቸው ወይም ይህ ስልት አያዋጣም ብለው ስላመኑ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ያስቀመጣቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች ባለመቀበል በመረጡት የትግል ሥልት የሚንቀሣቀሱ ናቸው።

የኢሠዴአኃ ም/ቤት አመራራቸው በውጭ በሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚነሣውን ጥያቄና ያለባቸውን ችግሮችና መሰናክሎች ይረዳል። ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን በአገር ውስጥ በግልጽ ተንቀሣቅሰው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ይታገላል። አገራችን ከጦርነት አዙሪት እንድትወጣና ዘላቂ ሠላምና መረጋጋት እንዲሰፍን በአገራችን [redacted] የሠላማዊ ትግል ባሕል እንዲዳብር ይታገላል። ይህ እውን የሚሆነው በሕዝብ ይሁንታ ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር እንዲኖር ነፃ፣ ትክክለኛና ርትዐዊ ምርጫ ሲኖር ነው። ለዚህ ግብ እስከመጨረሻው ይታገላል።

በመሆኑም ይህ ስብሰባ ተቃዋሚ ድርጅቶች ያለ ኃይልና የጠብመንጃ ትንቅንቅ አርበኝነት መኖሩን በኃይል ለሚያምነውና ለሚመካው ወያኔ/ኢሕአዴግ የሚያሣዩበት፣ የሠላማዊውን የትግል አቅጣጫ የሚመሩበት እና በእርሱ የተሣሣተ አቅጣጫ የሚጓዙ አለመሆናቸውን የሚያሣይ እንደሚሆን እንጠብቃለን።

3.3 <u>መደምደሚያ</u> :- <u>የኢሠዴአኃ ም/ቤት ከጉባዔው የሚጠብቀው</u>

የስብሰባውን አስፈላጊነት በምናምንበትና በምንቀበልበት ጊዜ ስብሰባውን አስፈላጊ ያደረጉት ነጥቦች ተገቢ ምላሽ አግኝተው የተጠናከረ ተከታታይ እንቅስቃሴ የሚደረግበትን ሁኔታ መፈጠር ም/ቤቱ ከጉባዔው [redacted]። ም/ቤቱ ከስብሰባበው የሚጠብቃቸው ውጤቶች በሦስት ይጠቃለላሉ። እነዚህም :-

1ኛ/ ስብሰባው የተቃዋሚ ኃይሎችን የትግል ኅብረት የሚያጠናክር ሥልት እንዲቀይስ ይጠበቅበታል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በአገራችን ያለውን የፖለቲካ ቀውስ ሥርዓት ለማስያዝና [redacted] ሠላማዊ የፖለቲካ ትግል ሥልት ለመተግበር የብሄራዊ እርቅ ጥያቄ ምላሽ የሚያገኝበትን ዘዴ ማፈላለግና ለተግባራዊነቱም ሥልት መቀየስ ይጠበቅበታል።

2ኛ/ ስብሰባው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄዎች በሠላማዊ ትግል በዴሞክራሲያዊ አግባብ ምላሽ የሚያገኙበትን የትግል ስትራቴጂና ታክቲክ መቀየስ ይጠበቅበታል። ይህም የሚመለሰው ሕዝብ በሚሣተፍበት ነፃ፣ ትክክለኛና ርትዓዊ ምርጫ ስለሆነ እ.ኤ.አ. በ2000 ዓ.ም. ለሚደረገው ምርጫ ተቃዋሚዎች የሚሣተፉበትን ሁኔታ ተወያይቶ ከአንድ ስምምነት እንዲደርስ ይጠበቃል።

3ኛ/ ስብሰባው ከተሣሣተ የመንግሥት ፖሊሲና ከአፈፃፀሙ በመነጨ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ከተከሰተው ጦርነት እና በደቡብ ኢትዮጵያ ከታየው ዓይነት የሕዝብ ግጭት እንድንወጣ፣ ለችግሩም ዘላቂ መፍትኼ ለማምጣት ይቻል ዘንድ ተቃዋሚዎች፣ መንግሥትና ሕዝቡ መውሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች አቅጣጫ መጠቆም ይጠበቅበታል።

አገራችን ከመቼውም የታሪክ አጋጣሚ የከፋ ችግር ውስጥ የማውጣት ኃላፊነት ከፊታችን ተደቅኗል። ይህን የሕዝብና የታሪክ ኃላፊነት ለመወጣት በመካከላችን ያሉትን ልዩነቶች አቻችለን፣ ከጥላቻ የፀዳ፣ ከጠባብ የድርጅት ስሜት የተላቀቀ፣ የግል ድብቅ ስሜትን ያሽቀነጠረ፣ በእርግጥም አገራችን ላለችበት አሣሣቢ ሁኔታ ቅድሚያ የሚሰጥና ዘላቂ መፍትኼ ለማምጣት የሚያስችል አቅጣጫ የሚያመለክተን ውጤት የሚያስጨብጥ ውይይት ማድረግ ይጠበቅብናል። ለዓላማችን መሣካት እያንዳንዱ የዚህ ስብሰባ ተሣታፊ ድርጅት ያለውን አስተዋጽኦ በመገንዘብ ከየድርጅቶቹ ለሚቀርቡ አስተያየቶችና የመፍትኼ ኃሣቦች ተገቢውን ትኩረት መስጠት ያለብን መሆኑ መጤን ይኖርበታል። ውይይታችን ከዚህ መንፈስ የተለየ ዓላማና ስሜት ካለው ሣይሆን በሕዝቡ የትግል ሞራል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ቸልሰን በችግራችን ላይ ችግር ጨምረን እንደባቢሎን ዘመን የጋራ ቋንቋ አጥተን በከንቱ ተጨጭቸን ሣንደማመጥ የምንለያይ ብቻ እንደምንበታተን ከወዲሁ ማስገንዘብ እንወዳለን። ይህ እንዳይሆን ሁላችንም ያለብንን ኃላፊነት ተገንዝበን የተሰበሰብንበትን ዓላማ እውን እንደምናደርግ የኢሠዴአኃ ም/ቤት ተስፋ ያደርጋል።

መስከረም፡ 01 ቀን፡ 1991 ዓ.ም.

ፓሪስ፡ ፈረንሣይ።